**የዕውነታ ወረቀት** | ህዳር 2022

# 15th Ave W/NW እና Ballard Bridge የማንጠፍ ፕሮጀክት

## የፕሮጀክት አጠቃላይ እይታ

15th Ave W/NW በሰሜን ምዕራብ ሲያትል የሚያገለግል ዋና መጋቢ መንገድ ነው። እንደ ቀረጥ ሲያትልን ለማንቀሳቀስ የማንጠፍ መርሃ ግብር አካል የሆነው የሲያትል የማመላለሻ መምሪያ (SDOT) የ15th Ave W/NW እና Ballard Bridge Deckን ከW Emerson St ወደ NW 57th St በፍጥነት እስከ 2023 በጋ ድረስ እየዘረጋ ነው። ፕሮጀክቱ ወሳኝ የሆነውን የሲያትል የመጓጓዣ አውታረ መረብ ሁኔታን ቀድሞ ወደነበረበት ይመልሳል እና እስከ 180 መስመር-ማይሎች መጋቢ መንገዶችን እስከ 2024 መጨረሻ ለማንጠፍ ለቀረጥ ያደረገውን ቁርጠኛነት ለSDOT አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ማሻሻያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- የሚነጠፉ አካባቢዎች በ15th Ave W/NW ላይ ከW Emerson እስከ NW 57th St
- በተመረጡ አካባቢዎች ከፕሮጀክቱ የማንጠፍ አካባቢዎች ጋር የእግረኛ መንገዶችን፣ ከሰፈር መውጫ የመኪና መንገዶችን እና የጎርፍ ውሃ የፍሳሽ መውረጃዎችን ማሻሻል
- የ15th Ave W/NWን ይዞ አሁን ባሉ ነባር ቦታዎች ላይ የእግረኛ መሻገሪያ ምልክቶችን እና የመንገድ ላይ ቅቦችን በአዲስ ቀለም እንደገና ማደስ
- በ15th Ave NW ላይ በNW 52nd St እና Market St መካከል ነባር ወደ ሰሜን አቅጣጫ የአውቶቡስ ብቻ መስመሮችን አዲስ ለመንገዶች የቀይ ቅቦችን መቀባት
- የድልድይ ማስፋፊያ መገጣጠሚያዎችን መተካት
- የሌሪ ዌይ ድልድይን (ከባላርድ ድልድይ እዚያው በስተሰሜን የሚገኝ) በማጠናከር የመሬት መንቀጥቀጥ ደህንነትን ማሻሻል




ለበለጠ መረጃ እና ለፕሮጀክት ኢሜይል ዝመናዎች ለመመዝገብ የፕሮጀክት ድህረ-ገጽን ይጎብኙ።


**የፕሮጀክት መረጃ እና ግንኙነት**
ጁልስ ፖሳዳስ (Jules Posadas)፣ የማዳረስ አመራር
15thAveW_NWpaving@seattle.gov ወይም (206) 651-3950
www.seattle.gov/transportation/15thAveBallardBridgePaving


Seattle Department of Transportation

The Levy to MOVE SEATTLE

## የፕሮጀክት መርሐግብር*

**ሚያዝያ 2022:** ቀደምት ንድፍ

**ጳደይ 2023:** ንድፍ

**በጋ 2023:** ግንባታ

**በልግ 2024:** ማጠናቀቅ

* በአቅርቦት መገኘት እና በአሰከፊ የአየር ሁኔታ ምክንያት መርሃ ግብሮች ሁል ጊዜ ሊለወጡ ይችላሉ።

## የፕሮጀክት ዳራ

ደህንነታቸው የተሻለ፣ ለስላሳ እንዲሆኑ እና የጥቅማቸውን ዕድሜ ለማራዘም በየአመቱ፣ በመጥፎ ሁኔታ ላይ ያሉትን መጋቢ መንገዶች ንጣፍ እናለብሳለን። የመጓጓዣ ስርዓታችንን በጥሩ የጥገና ሁኔታ ማቆየት የወደፊቱን የጥገና ወጪ ለመቀነስ ይረዳል። የመንገድ ንጣፍ ሁኔታን፣ የትራፊክ መጠንን፣ የሰነ መልክአ ምድራዊ ፍትሃዊ እኩልነትን፣ ወጪን፣ እና በገንዘብ ሰጦታዎች እድሎች ወይም በአካባቢው ካሉ ሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በማስተባበር ላይ በመመሰረት ለማንጠፍ ስራ ቅድሚያ እንሰጣለን።

## ከእርሰዎ መሰማት እንፈልጋለን

እባኮትን የዳሰሳ ጥናታችንን ይውሰዱ እና 15th Ave W/NW እና በባላርድ ድልድይ ፕሮጀክት ኮሪደርን ይዞ ስለሚያደርጉት የመዘዋወር እና የጉዞ ፍላጎቶች ያሳውቁን። በግንባታ ወቅት ለነዋሪዎች እና ንግዶች የጉዞ ተጽእኖን ለመቀነስ እንዲረዳን አጭር የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ የQR ኮዱን ይቃኙ ወይም www.surveymonkey.com/r/6YQSRG9 ን ይጎብኙ። የዳሰሳ ጥናቱ እስከ ጥር 13 ቀን 2023 ክፍት ሆኖ ይቆያል።